QuickNotes mcps

በ2014 ለMCPS ተማሪዎች BACKpacks (የጀርባ ቦርሳ) ስጧቸው

የ2014 MCPS GIVE BACKpacks (ቦርሳ ስጡ) ዘመቻ በወጉ ተጀምሯል እናም ችግር ላላቸው ተማሪዎች በት/ቤት አቅርቦቶች የተሞሉ የጀርባ ቦርሳዎች ለመግዛት ገንዘብ ለመሰብሰብ የርስዎን እርዳታ እንፈልጋለን።

የGIVE BACKpacks ዘመቻ የተጀመረው በMontgomery County እያደገ ለመጣው ችግር አፀፋ ለመመለስ በ2013 ነው። በርካታ ቤተሰቦች ፍይናንሳዊ ትግል አጋጥሟቸዋል እናም ለልጆቻቸው የት/ቤት መገልገያ ቁሳቁስ ማቅረብ ላይ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ባሁኑ ወቅት 51,000 የMCPS ተማሪዎች ነፃና የቅናሽ ዋጋ ምግብ በመቀበል ላይ ናቸው – የድህነት አመልካች።

ባለፈው አመት የMCPS ወላጆች፣ የት/ቤት ሰራተኞችና የማህበረሰብ አባላት በቸርነት ለGIVE BACKpacks ዘመቻ ከ$100,000 በላይ ሰጥተዋል፣ እንዲሁም 15,000 ተማሪዎች የት/ቤት አቅርቦቶች የተሞሉ የጀርባ ቦርሳዎች ተቀብለዋል። በዚህ አመት ይበልጥ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ለማገልገል ተስፋ አለን።

የ$10 ስጦታ አንድን የተቸገረ ተማሪ፣ በት/ቤት አቅርቦቶች የተሞላ፣ አንድ አዲስ ቦርሳ ያስገኝለታል። እንዲሁም በሚከተሉት ደረጃዎች የመስጠትም አማራጮችም አለዎት።

$300 – ለአንድ ክፍል ተማሪዎች ቦርሳዎች ያቀርባል

$1,500 – ለአንድ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ቦርሳዎች ያቀርባል

$6,500 – ለሞላ ት/ቤት ተማሪዎች ቦርሳዎች ያቀርባል

$25,000 እና ከዚያ በላይ – ላንድ ክለስተር ቦርሳዎች ያቀርባል *(ለተወሰነ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶችና ኮንሰሺየም ት/ቤቶች መጋቢ የሆኑ የኤሌሜንታሪና የመካከለኛ ት/ቤቶች)*

ይበልጥ ለመማር ወይም ለመስጠት ድርጣብያ www.mcpsgivebackpacks.org ይጎብኙ ወይም 301-309-MCPS ይደውሉ።

QuickNotes mcps

## የት/ቤት መዘግየቶችና መዘጋቶች፡ የMCPS ሂደት

ዊንተር ወይም አስከፊ የአየር ጠባይ ሲያጠቃ፣ ት/ቤቶችን የማዘግየት ወይም የመዝጋት ውሳኔ በMCPS በሞላ በደርዘኖች የሚቆጠሩ ሰዎችና መምርያዎችን ያካትታል። በት/ቤቶች Superintendent ውሳኔ አንዴ ከተወሰደ በኋላ፣ ለMCPS ማህበረሰብ በተለያዩ መንገዶች ይተላለፋል። ስለ ሂደቱ ይህን ቪድዮ በመመልከት የበለጠ ተማሩ። http://www.montgomeryschoolsmd.org/mainstory/story.aspx?id=353913

## ማሻሻያ ስለ MCPS Snow Days (በረዶ ቀኖች)

በዚህ አመት በዋሺንግቶን፣ ዲሲ አካባቢ የታየው የዊንተር አየር ጠባይ የተማሪዎችንና የት/ቤት ሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ የአካባቢውን የት/ቤት ዲስትሪክቶች በርካታ "snow days (የበረዶ ቀኖች)" እንዲያውጁ መርቷቸዋል። በመጥፎ አየር ምክንያት የጎደሉትን የትምህርት ቀኖች የMontgomery County Public Schools እንዴት አድርጎ እንደሚተካቸው በርካታ ጥያቄዎች ለሰራተኞቹ ደርሰዋቸዋል። የተሟላ ማብራርያ ይኸውና፡-

የሜሪላንድ ስቴት የት/ቤት ዲስትሪክቶች 180 የትምህርት ቀኖች እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። በMontgomery County የትምህርት ቦርድ ለMCPS የፀደቀው የ2013-2014 የትምህርት ቀን መቁጠርያ፣ 184 የትምህርት መስጫ ቀኖች ያካትታል፣ ይህም ማለት አራት የአስቸኳይ አየር ሁኔታ (ወይም "snow days (የበረዶ ቀኖች)") ቀን መቁጠርያው ላይ ታስበዋል ማለት ነው። የቀን መቁጠርያው በተጨማሪ MCPS ከአራት በላይ የበረዶ ቀኖች ካጋጠመው ትምህርት ሊሰጥባቸው የሚቻል አምስት "መጠባበቂያ" ቀኖች አካትቷል። ዲስትሪክቱ ስቴቱ የሚጠይቀውን ዝቅተኛውን ቀኖች ያሟላ ዘንድ እነዚህ የመጠባበቂያ ቀኖች በትምህርት አመት መጨረሻ ላይ እንዲታዩ ይደረጋል። የመጠባበቂያ ቀኖቹን በትምህርት ቤቱ የቀን መቁጠርያ ታች መጨረሻ ላይ ልታይዋቸው ትችላላችሁ።

በዚህ አመት እስከ ዛሬ ድረስ (እስከ ማርች 14 2014)፣ MCPS ዘጠኝ የበረዶ ቀኖች ነበሩት፣ የህም ማለት የቀን መቁጠርያው ውስጥ ከተያዘው በአምስት ቀኖች አልፈናል

ማለት ነው። ለMCPS ፕሮግራም የተደረገው የመጨረሻ የትምህርት ቀን ሀሙስ፣ ጁን 12 ነበር። በስቴት በኩል ህጋዊ ለውጥ እስካልተደረገ ድረስ፣ የስቴቱን የ180-ቀን ድንጋጌ ለማክበር የመጨረሻው ቀን ወደ ሀሙስ፣ ጁን 19 መንፏቀቅ ይኖርበታል። በዚህ አመት ተጨማሪ የበረዶ ቀኖች ካጋጠሙን፣ የትምህርት ቦርድ ባፀደቀው የቀን መቁጠርያ መሰረት፣ የት/ቤት የመጨረሻ ቀን በተጨማሪ ወደ ኋላ መገፋት ይኖርበታል። የስፕሪንግን የእረፍት ጊዜ ለመለወጥ ምንም እቅዶች የሉም።

ዲስትሪክቱ ከ180-ቀን ግዳጅ ለመቀነስ እንዲችል ለሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ ህጋዊ ማስወገጃ ለማግኘት ማመልከት ይችላል። ለማስወገጃ ስለማመልከት ውሳኔ የሚደረገው በኋላ በአመቱ መጨረሻ ላይ ነው፣ ዲስትሪክቱ ምን ያህል የበረዶ ቀኖች እንደነበረው ካረጋገጥን በኋላ። ምንም እንኳን እንደዚህ አይነቶች ማስወገጃዎችን ዲስትሪክቱ ከዚህ በፊት የተቀበለ ቢሆንም፣ በዚህ አመት ሊቀበል ይችላል የሚያሰኝ ዋስትና የለም።

የሜሪላንድ ገቨርነር Martin O'Malley (ማርቲን ኦ'ማይሊ) በፌብሩ. 13 እና 14 የስቴት ያስቸኳይ ጊዜ የማወጁ እውነታ ለነዚህ የበረዶ ቀኖች መስወጋጃ ሊያሰጥ ይችላል ቢያሰኝም፣ ዋስትና ግን የለም። ዲስትሪክቱ አሁንም ቢሆን ለማገኛው ማመልከት የግድ ይኖርበታል።

ለስፕሪንግ ቲያትር ምርቶች ቲኬቶቻችሁን አግኙ

በመላ የት/ቤት ስርአት፣ በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶችና በ2ኛደረጃ ት/ቤቶች በሁለቱም፣ በስፕሪንግ የትያትር ምርቶች መጋራጃው በመነሳት ላይ ነው። ማርች መባቻ አካባቢ ጀምሮ እስከ ሜይ የሚካሄዱት ታላላቅ ትያትር ስራዎችን ለማየት ከአሁኑ ፕላን አድርጉ። ከ"Macbeth" እስከ "Hairspray"፣ ለሁሉም የሚሆን በያይነቱ አለ።

[የስፕሪንግ ትያትር ትርእይት ፕሮግራም]()

የሰመር ት/ቤት ክፍያዎች ለ2014 ተወስኗል።

የትምህርት ቦርድ የሰመር ት/ቤት ክፍያ ለሚመጣው ሰመር አፀደቀ፣ ክፍያውም ካለፈው አመት ክፍያ ጋር ተመሳሳይ ነው። ሙሉ ክፍያዎች $355 ለኤሌሜንታሪ ኮርሶች፣ $300 ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መሰረታዊ ኮርሶች፣ እና $310 ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት የመስመር ላይ ኮርሶች፣ የተማሪ መስመር ላይ ትምህርትን ጨምሮ፣ ሆነው ይቀጥላሉ። ቅናሽ ክፍያዎች $85 ወይም $120፣ እንደ ቤተሰብ ገቢ መጠን፣ ሆነው ይቀጥላሉ።

በአራት የኤሌሜንታሪ ያካባቢ ማእከሎች፣ አራት የ2ኛ ደረጃ ያካባቢ ማእከሎች፣ እና ያካባቢ የት/ቤት ፕሮግራሞች አማካኝነት MCPS የሰመር ት/ቤት ፕሮግራሞች (Summer School programs) ለጣልቃገብነት፣ ብልፅግና እና የተጣደፈ አከዴሚያዊ ትምህርት ለMCPS ተማሪዎች ያቀርባል። ምዝገባ ኤፕረል 3 2014 ለመጀመር ታቅዷል።

[የሰመር ትምህርት]

Ride On አዲስ የወጣቶች የSmarTrip ካርድ ፕሮግራም ጀመረ

Ride On የአውቶቡስ አገልግሎት ወደ አዲስ Youth Cruiser SmarTrip Card (የወጣት የረጅም አገልግሎት ካርድ) በመሸጋገር ላይ ይገኛል። ወርሀዊዎቹ የይለፍ ወረቀቶች አገልግሎታቸው ፌብሩዋሪ ላይ አከተመ እናም ተማሪዎች አሁን በአዲሱ Youth Cruiser SmarTrip ካርድ ወርሀዊና የሰመር ማለፊያዎቻቸውን መሙላት አለባቸው። በማርች 1 እና በጁን 30 መካከል፣ እድሜአቸው 18 እና ከዚያ በታች የሆነ የMontgomery County ነዋሪዎች፣ የት/ቤት መታወቂያቸውን ወይም Youth Cruiser SmarTrip በማሳየት በስራ ቀን ከ2 p.m. እስከ 7 p.m. በነፃ መጓዝ ይችላሉ። በተቀሩት ጊዜዎች በሙሉ፣ ልጆች በYouth Cruiser SmarTrip ካርድ አማካኝነት መጠቀም ወይም በጥሬው መክፈል አለባቸው። Youth Cruiser SmarTrip ካርድ በሚከተሉት ቦታዎች መግዛት ትችላላችሁ።

TRiPS Store, 8413 Ramsey Avenue, Silver Spring, 240-773-8747
TRiPS Store, 17 Wisconsin Circle, Friendship Heights, 240-773-8747
Treasury Division, 255 Rockville Pike, Suite L-15, Rockville,
240-777-8930

ለተጨማሪ መረጃዎች፣ Ride On Transit Systemን 240-777-5870 በመደወል፣ ወይም Facebook እና Twitter ገፆች በመጎብኘት መገናኘት ትችላላችሁ።

**የምርጫ ቀን ቡድን አባል ሁኑ**

Montgomery County Board of Elections Future Vote Initiative (የምርጫና የወደፊት ድምፅ መስጠት ቅስቀሳ ቦርድ) ማክሰኞ፣ ጁን 24 ለሚካሄደው የ2014 የሜሪላንድ ገቨርነር ተቀዳሚ ምርጫ የምርጫ ቀን ረዳቶች ሆነው ያሚያገለግሉ ከ6ኛ እስከ 12ኛ የሚገኙ ተማሪዎች በማፈላለግ ላይነው። በረዳትነት የሚያገለግሉ ተማሪዎች Student Service Learning (የተማሪ የመማር አገልግሎት) (SSL) ሰአቶች ይቀበላሉ። በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው አስገዳጅ የሆነ የስልጠና ስብሰባ መከታተል አለባቸው። የምዝገባ የቀን ገደብ ሰኞ፣ ኤፕረል 14 ነው። ለተጨማሪ መረጃዎች ድርጣብያ ይጎብኙ፣ ወይም ወደ uture.vote@montgomerycountymd.gov ኢሜይል ያድርጉ።

**Trades Foundation የመኪና ስጦታዎች ይፈልጋል**

የMontgomery County Students Automotive Trades Foundation (የተማሪዎች የመኪና ጥገና ድርጅት) (ATF) የመኪና ስጦታዎች እየፈለገ ነው። ስጦታዎች 350 የሚደርሱ የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤት ተማሪዎችን መኪናዎችን መመርመር፣ መጠገንና ማደስ ለመማር ሊያግዛቸው ይችላል። ATF ለተማሪዎች የእንክብካቤ፣ የጥገና፣ የሽያጭና የግብይት ተግባራዊ ስልጠና በመስጠት የመኪና ምህንድስና (automotive) ትምህርት የሚሰጥ በጎ አድራጎት ነው። መኪኖችን የautomotive ፕሮግራም ባላቸው በDamascus፣ Gaithersburg፣ Seneca Valley ወይም Thomas Edison የ2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች መስጠት ይቻላል። ሰጭዎች የታክስ ቅናሽ የማግኘት ብቃት አላቸው።

ለተጨማሪ መረጃ፣ የATF ድር ጣብያ ይጎብኙ እና Donate Your Car የሚለውን ትር ጠቅ አድርጉ። ወይም፣ Mike Snyder (ማይክ ስናይደር)ን በ301-929-2164 ተገናኙ።